# በምሥራቅ ወለጋ 30 አርሶአደሮች በኦነግ ሸኔ ታፍነው መወሰዳቸው ተነገረ

By እመቤት አክሊሉ - 28/11/2021




በምሥራቅ ወለጋ ጊዳ ወረዳ ከ 30 በላይ አርሶ አደሮች ታፍነው መወሰዳቸውን የአካባቢው ነዋሪዎች ተናገሩ። ነዋሪዎቹ ለአዲስ ማለዳ እንደገለጹት፣ ኅዳር 14/2014 ከጠዋቱ 12 ሰዓት፣ የአንገር ጉቴ ሌሊሳ መካኒሳ ቀበሌ ነዋሪዎች፣ ሰብል ለመሰብሰብ በሄዱበት ታፍነው ቀርተዋል። ከ200 በላይ የሆኑ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች ተኩስ ከፍተው አርሶ አደሮቹን አፍነው ወዳልታወቀ ጫካ እንደወሰዷቸው ታውቋል።

በአካባቢው ውጥረት የጀመረው ከመስከረም 16/2014 ጀምሮ እንደሆነ ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገ የቀበሌው ነዋሪ ተናግሯል። ኦነግ ሸኔ በጉትበን ወረዳ በሚኖሩ ሰዎች ላይ በዚሁ ቀን በከፈተው ተኩስ ኹለት ሰዎች መገደላቸውን ተከትሎ፣ 800 አባውራዎች ቤተሰቦቻቸውን በመያዝ ወደ አንገር ጉቴ ሌሊሳ መካኒሳ ቀበሌ ለመሸሽ ተገደዋል።

አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ ሕይወቱን በግብርና የሚመራ በመሆኑ፣ የዘሩትን ሰብል መሰብሰብ እንዳልቻሉ አስተያየት ሰጭዎቹ ጠቁመዋል። ሕይወትን ማትረፍ ከንብረት፣ ከሰብል ይበልጣል ያሉት እነዚሁ ተፈናቃዮች፣ ”ከኹለት ወር በላይ ከቀያችን ወጥተን በዚሁ ቀበሌ ብንኖርም፣ ረሀቡን መቋቋም ስላቃተን ኅዳር 14/2014 ወደ እርሻ ሔደን ሰብሉን ለመሰብሰብ ስንሞክር ያልታሰበ አደጋ ደረሰብን” በማለት ምሬታቸውን ተናግረዋል። “ረሀብ ጊዜ አይሰጥም፤ ልጆቻችን በረሀብ ሲያልቁ በአይናችን ከማየት፣ የመጣው ይምጣ” በማለት ወደ ማሳቸው ሔደው የደረሰውን በቆሎ ለመሰብሰብ ሲሞክሩ፣ “በድንገት የመጡ፣ በግምት ወደ 200 የሚሆኑ የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች ድንገተኛ ተኩስ በመክፈት ጓዶቻችንን አፍነው ወስደዋቸዋል” ሲሉ የሆነውን አስረድተዋል። አያይዘውም “የተቀረነው እግሬ አውጪኝ በማለት ወደተጠለልንበት ቀዬ ለመመለስ ችለናል” በማለት ከአደጋው የተረፉት አርሶ አደሮች ስለሁኔታው አስረድተዋል።

ቅሬታ አቅራቢዎቹ ፣ የታገቱት አርሶ አደሮች ጋር በተደጋጋሚ ሲደውሉ፣ የኦነግ ሸኔ አባላት ስልኩን በማንሳት፣ “እሬሳችሁን መጥታችሁ አንሱ”፣ ከቆይታ በኋላ ደግሞ፣ ”ገንዘብ አምጡ እና የታገቱትን ተረከቡ” በማለት እንደመለሱላቸው ለአዲስ ማለዳ ተናግረዋል።

በወቅቱ የአካባቢው ሚሊሻ፣ ሕዝቡንና አካባቢውን ከአደጋ ለመከላከል በሚሞክርበት ጊዜ በአካባቢው ተሰማርቶ የነበረ የመከላከያ አዛዥ ሚሊሻውን መልሶ እንዳያጠቃ መከልከሉን የአካባቢው ነዋሪዎች የገለጹ ሲሆን፣ መንግሥት ሕዝብ የመጠበቅ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

ነዋሪዎቹ ፣ በጉትበን ወረዳ የመከላከያ ካምፕ ውስጥ በርካታ ሠራዊት መኖሩን ገልጸው፣ የመከላከያ ሠራዊቱ ግን ነዋሪዎቹን ከጥፋት ሊያድናቸው አልቻለም ብለዋል። መከላከያው “ትዕዛዝ አልመጣም” ከማለት ውጪ፣ ለነዋሪዎቹ ተገን መሆን እንደተሳነው ተናግረዋል።

አስተያየት ሰጭዎቹ አክለውም፣ ኦነግ ሸኔን በመሸሽ ቀያቸውን ለቀው በመካኒሳ ቀበሌ የሚኖሩት ነዋሪዎች ከ 15 ሺሕ በላይ መሆናቸውን ገልጸው፣ የትኛውም የመንግሥት አካል ተመልክቷቸው ወይም ዕርዳታ አድርጎላቸው እንደማያውቅ አስረድተዋል፡፡

---

**ተጨማሪ ጽሑፎች:**

- የከተሞች መስፋት ያፈናቀላቸው አርሶ አደሮች ካሣ - መልሶ ማቋቋም - ስጋት
- የከተሞች መስፋት ያፈናቀላቸው አርሶ አደሮች ካሣ - መልሶ ማቋቋም - ስጋት
- የኦዴፓ እና ኦነግ ጫማ መለካካት! "የኦነግ ሠራዊት" ለዳውድ ኢብሳ ይታዘዛል ወይ?

---

መፈናቀላቸው ዕውቅና እንዲሰጠው በመንግሥት አካል ባለመፈለጉ ምክንያት፣ ሕዝቡ ለከፋ ረሀብ እና እንግልት መዳረጉን ተፈናቃይ አባውራዎቹ ጠቁመዋል፡፡ በድህነት ላይ ግድያ ለምን ዕጣ ፈንታችን ይሆናል የሚሉት እኒህ ዜጎች፣መንግሥት ባለበት አገር እንደዚህ በሰው ልጆች ላይ ይደርሳል ተብሎ የማይታሰብ ግፍ መድረሱ እጅግ ያስመርራል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ይህንን አስመልክቶ አዲስ ማለዳ ፣ ለጉተበን ወረዳ የጸጥታ ኃላፊ ኩምሳ መኮንን ብትደውልም፣ ስልኩ የተሳሳተ መሆኑን በቁጣ በመመለስ ዘግተውታል፡፡ ከፌዴራልም፣ ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን እና ኦሮሚያ ኮሚዩኒኬሽን ኃላፊ በኩል መልስ ለማግኘት ከአዲስ ማለዳ በተደጋጋሚ ስልክ ብትደወልም መልስ ማግኘት አልቻለም፡፡

---

ቅጽ 4 ቁጥር 160 ሕዳር 18 2014

**እመቤት አክሊሉ**

*http://addismaleda.com*

## ስለ እኛ

አዲስ ማለዳ ወቅታዊ የአገራችንን ጉዳዮች በስፋትና በጥልቀት የምትተነትን፣ እንዲሁም የተረጋገጡና የትም ያልተሰሙ ዜናዎች የሚቀርቡባት የብዙኃን መገናኛ ናት፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚዲያ ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 241/2010 ተመዝግባለች፡፡

ያግኙን: info@addismaleda.com

## ይከታተሉን